**March 5, 2007**

**በሺህ ዓመት አንድጊዜ ብቻ!**

**በሺህ ዓመት አንድጊዜ ብቻ የሚመጣዉን የኢትዮጲያ ሚሊኒየም በዓል አከባበር በማስመልከት ለ ሁለት ወራት ያህል ተቋቁሞ ስራዉን ሲያካሂድ የቆየው ኮሚቴ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የሚገኙትን ህዝባዊ ድርጅቶች፤ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሃይማኖት ተቋማት፤ የሬድዮ የቲቪና የጋዜጣ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች፤ የሴቶችና የወጣት ድርጅቶች የኢትዮጲያ ማህበረሰብ አገልግሎት ተቋሞች፤ የአርቲስቶች ማህበር፤ የስፖርት ፌዴሬሽን የመሳሰሉትንና በግለሰብ ደረጃም ጭምር ያካተተ ሰፊ ስብሰባና ጥሪ አድርጐ** Feb 27, 2007 **በ በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው** Unification church **ያካሄደዉን ስብሰባ በጥሩ ዉጤት አጠናቀቀ።**

**ወደ 25 የሚጠጉ ልዩ ልዩ ዕውቅ ግለሰቦችና የድርጅት ተወካዮች በተገኙበት በዚሁ ስብሰባ ላይ ኮሚቴው የበዓሉን ዓላማና ዝርዝር ፕሮግራም የሚከበርበትን ምክንያትና ታሪካዊ አመጣጥ በማስረዳት ለበለጠ ዉጤትና መጠናከር የሁሉም ኢትዮጲያዊ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ በመጠቆም የተሰሩትን ዝርዝር ስራዎች አስረድትቷል። ኮሚቴዉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊና ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ስራዎች ያከናወነ ሲሆን በመላው ሰሜን አሜሪካ የተዋቀሩትትን ኮሚቴዎችና አባላት አስተዋዉቋል። የተገኙትም እንግዶች በኮሚቴዉ ሰፊ ስራ ያላቸውን አድናቆት ገልፀው በበለጠ ሰፋ ብሎ ምክርቤት መስርቶ በመተዳደሪያ ደንብ ተጠናክሮ መቀጠሉ ጠቃሚነቱን አውስተዋል። በተለይም በግለሰብ ደረጃ ዝግጅቱን ከማደናቀፍ ሁሉም በሚችለው በሚፈቅደው ወይም በበለጠ ሊያገለግል በሚችልበት ኮሚቴ ገብቶ እንዲሰራ አሳስበዋል። በቃላትና በሀሳብ ረገድም አንዳንድ እርማቶች እንዲደረጉ ጠቅሶ ከሚጠበቀው በላይ ለተከናወኑት ድርጊቶች ምስጋናቸዉን ለግሰዋል።**

**በታቀዱት ስራ ዘርፎች መሐከል የሽልማት  ዝግጅት እንዲካተት ሃሳብ ቀርቦ በሚገኘዉ ውጤት ኮሚቴው ተጠቃሚ እንዲሆንና አሁንም እንኳን ያለምንም ገንዘብ ትርፍ በዝግጅቱ መኖር ብቻ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ መሆኑን አዉስተዋል። ባለው የጊዜ እጥረት አኳያ ሥራው እየተሰራ እንዲቀጥልና የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመንደፍና ወደህብረተሳቡ በመሄድ ለማሰባሰብ የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት የሁሉም ሥራ መሆኑን አስታውቆዋል። የሬድዮ የቲቪ የጋዜጣ ባለሞያዎች ይህንን ትልቅ ዓላማ በማሳወቅ እንዲረዱና ከህዝቡ ፍላጎት ውጭ የወያኔን መንግሥት ዓላማ የሚያራምዱ ሌሎች ዝግጅቶችን በግልፅ ማውገዝ እንደሚገባ ወስነዋል። በተፈለገዉ ሁሉ በጋራ ለመሥራት ተስማምተው ለሚቀጥለው** March 13, 2007 **ስብሰባ እንዲኖር ተወስኖ ተለያይተዋል።**

www.ethiopianmillennium2000.com
www.2kethiopia.com